የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF LABOUR AND SOCIAL AFFAIRS - ETHIOPIA

# ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ሥራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ 811/2013 ማሻሻያ አስመልክቶ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

2013ዓ.ም

አዲስአበባ

## የመመሪያው ማሻሻያ አስፈላጊነት

ሴት ሠራተኞች ከተፈጥሮ ባህሪያቸው አንጻር በስራ ቦታቸው ልዩ ጥበቃና ክትትል የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው ቀደም ሲል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 መሠረት አድርጎ በ2005 ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር እንዲገባ ተደርጎ የነበረው ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጉጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ሥራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ በስራ ቦታዎች የነበሩበትን የተፈፃሚነት ውስንነቶች ለማስተካከል እንዲሁም በመመሪያ ያልተካተቱና በስራ ቦታ መተግበር ያለባቸውን ለማካተት እና የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 1156/2011 ዓ.ም በመሻሻሉ ሴት ሰራተኞችን ጤንነት ለማስጠበቅና ከስራ ባህሪያቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ወይም ከሥራ ሂደት የሚመነጩና በሴት ሠራተኞች ላይ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት የማስከተል ውጤት ያላቸው ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ስነ ሕይወታዊ፣ ኢርጉኖሚካልና ሳይኮሶሻል ጠንቆች በተሻለ ሁኔታ ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት መመሪያውን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

## የመመሪው መሻሻል ሂደት

በሚ/ር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የመጀመሪያ ረቂቅ የመመሪያ ማሻሻያ ላይ ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፤ ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ኮንፌዴሬሽን ፣ ከኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌደሬሽን በፅሁፍ የተሰጡ አስተያቶችን በማሰባሰብ ረቂቅ መመሪያውን የማዳበር ስራ ከተሰራ በኋላ እነዚህን አካላትን በመጥራትና በተጨማሪም ከኢዲስ አበባ ዩኒቨርስት ፤ ከትምህርት ሚኒስቴር ከሴቶች ጉዳይና ከጤና ሚኔስቴር ከተውጣጡ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብዓቶችን በማሰባሰብ መመሪያውን የመጨረሻ መልክ የማስያዝ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመጨረሻም ለሚኒስትር መ/ቤቱ ማኔጅመንት አባላት ቀርቦ በተደረገ ውይይት ዳብሮ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

## <u>መመሪያው ዝርዝር ድንጋጌዎች</u>

መመሪያው 13 አንቀፀች ያሉት ሲሆን ከ1 እስከ 4 ያሉት አንቀፆች አጠቃላይ ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም መመሪያው "ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጉጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ሥራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ "ተብሎ አጭር ርዕስ ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ትርጓሜ በያዘው አንቀፅ 3 በመመሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ቃላትና ሀረጎች ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡

በመቀጠል በአንቀፅ 4 ላይ የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰንን የሚደነግግ ሲሆን በዚህም መመሪያው የአዋጁ ማስፈፀሚያ ከመሆኑ አንፃር የመመሪያው ተፈፃሚነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 በሚሸፈን በቅጥር ላይ በተመሠረተ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ላይ መሆኑ ተደንግጓል፡፡

ከአንቀፅ 5-7 ያሉት አንቀፆች ላይ ሴቶች እናት በመሆናቸው በተለይም ነፍሰ ጡር የሆኑትና የሚያጠቡ ሴት ሠራተኞችን የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር ከሚያሥከትሉና የፅንስ ተፈጥሮአዊ ዕድገት ከሚያዛቡ የሙያ እና የጤና ጠንቆች ለመከላከል እንዲቻል በአንቀፅ 5 ሴት ሰራተኞች ሙሉ ለሙሉ እንዳይሰማሩባቸው ወይም ሴት ሰራተኞችን ቀጥሮ ማሰራት የተከለከሉ ስራዎች ዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን በሌላ በኩል በአንቀፅ 6 አሰሪው ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ በማድረግ ማለትም ከተቀመጠ ደረጃ በላይ እንዲሰሩ ባለማድረግ ፣ አመታዊ የጤና ምርመራ እየተደረገላቸው ሴት ሰራተኞች ሊሰሩባቸው የተፈቀዱ የሥራ ዝርዝሮች ተደንግገዋል፡፡ ሆኖም በመመሪያው በአንቀፅ 5 እና 6 በተዘረዘሩ ሥራዎች ላይ ነፍሰጡር ሠራተኞችና ከወሊድ በኋላ እስከ 6 ወራት ድረስ የሚያጠቡ ሠራተኞች ማሰራት የተከለከለ መሆኑ በአንቀፅ 7 ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪ ሴት ሠራተኞችን ጉልበት በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ ፣ የመሸከም ፣ የማጓጓዝ ፣ የማንሳት ፣ የማውረድ ፣ የማውጣት ፣ የመጎተት ፣ የመሳብና የመሳሰሉት ሥራዎች ላይ ሲሰማሩ ስራዎቹን የሚያከናውኑበትን መንገድ ማለትም በእጅ ሲሆን፣ በእጅ ሆኖ ዳገት የመውጣትና የመውረድ ሲኖር፣ስራው ባለአንድ እግር ወይም ባለሁለት እግር ጋሪ በመታገዝ የሚከናወን ሲሆን በሚል በመከፋፈል ለእያንዳንዱ የተፈቀደ የክብደት መጠን ጣሪያ በማስቀመጥ ሴት ሰራተኞች ክብደት

ያለውን እቃ ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ ምክንያት ሊደርስ ከሚችል የጤና ችግር ጥበቃ የሚያገኙበት ሁኔታ በአንቀፅ 8 ተደንግጓል፡፡

ሴት ሠራተኞች በተሰማሩባቸው ሥራዎች ሳቢያ ሊደርስባቸው የሚችሉ ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ስነ ሕይወታዊ፣ ኢርጉኖሚካልና ሳይኮሶሻል ጠንቆች ለመከላከል በመመሪያው የተቀመጡትን ክልከላዎችንና ጥበቃዎችን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር አሰሪው ላይ የተጣሉ ሀላፊነቶች በአንቀፅ 8 የተዘረዘሩ ሲሆን በተጨማሪም በአሰሪው በኩል የመመሪያው መጣሰ ሲኖር በአዋጁ የተቀመጡት የቅጣት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በአንቀፅ 10 ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ከአንቀፅ 11–13 አጠቃላይ ድንጋጌዎ የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም ለመመሪያው ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ፣መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ እና የቀድሞ በ2005 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው መመሪያ የተሻረ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡